ኢትዮጵያን ጨምሮ የአፍሪካ አገሮች የተጋፈጡት አዲስ የደኅንነት አደጋ

በዮናስ አማረ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ (ዶ/ር) እና ክፍተኛ የመንግሥት አመራሮች የልር ዓባይ ድርን ማምረታን ሲገበኙ

እ.ኤ.አ. በ1849 የኦስትሪያ ኃይሎች የቬነስ ከተማን የማውደም ተልዕኮ ያዘጋጃሉ። በአየር ላይ በሚንሳፈፉ ትልልቅ ፊኛ (ባሉን) በምብ ጭኖ ከሰማይ ወደ መሬት በማዝነብ ከተማዋን እንዳልነበረች አድርጎ የማውደም ተልዕኮ ነበር ኦስትሪያኖቹ የዘየዱት። ለተልዕኮው እስከ 30 ባሉኖች ተሳኩ። ይሁን እንጂ የአየር ጠባዩ ኃይለኛ ግፊት ያለው ንፋስ የበዛበት ስለነበር አንድ ቦምብ (ተቀጣጣይ ነገር) ብቻ ነበር ቬነስ ከተማ ላይ የወደቀባት።

የኦስትሪያዊያኑ ባሉኖች በአየሩ ተለዋዋጭነት የተነሳ ዓላማቸውን እንደታቀደው ሳይመቱ ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ መክሸፋቸው ይነገራል። ይሁን እንጂ ይህ ዘመቻ ከዚያ በፊት በታሪክ ተሞክሮ የማያውቅ የጦር ዕቅድ፣ አዲስ የጦር መሣሪያና አዲስ የጦር ሥልት እንዲፈጠር መነሻ መሆኑ ይነገራል። የሰው ልጆች ሰው አልባ በራሪ ተዋጊ (ድሮን) ፈጥሮ የመዋጋት ሐሳብን እንዲህ ካለው የታሪክ አጋጣሚ መቅዳታቸው

ነው። ድሮን መንግሥታት የሚኩራሩበት ብቻ ሳይሆን፣ እዚህም እዚያም የመሸጉ የትጥቅ ቡድኖች የታጠቁትና የሚፈጽሙበት



በግለሰቦች እጅ የገባ ቴክኖሎጂ ሆኖ ይገኛል። ለዕቃ ማመላለስ፣ መረጃ ማሰባሰብ፣ ለመድኃኒትና ክትባት ማጓጓዝ፣ ለፀረ ተባይና ርጭት ለአርሻ ሥራዎች ጨምሮ ለበርካታ በጎ የልማት ሥራዎች የሚውለው ድሮን ዋና በድምፅና ምሥል ቀረፃ አጋር በመሆንም ለሚዲያ ዘርፍ በሰፊው ጥቅም ላይ መዋሉ በአዎንታዊነት ይነሳል።

ሆኖም በተቃራኒው ለጦርነት ቴክኖሎጂው ከፍተኛ ግልጋሎት መስጠት የሚችል መሆኑ ደግሞ፣ በርካታ ውድመትና ዕልቂት ባስከተሉ ግጭቶች ውስጥ በሰፊው እንዲውል እያደረገው ነው።

በቅርብ ዓመታት ሊቢያ የድሮን መሣሪያ ውጊያ መሞከሪያ ሆናለች። በአዘርባይጃንና በአርሜኒያ መካከል በተካሄደው የናጎሮ ካራባህ ጦርነት በሰፊው የዋለው ድሮን፣ በዩክሬንና በሩሲያ ጦርነትም ውስጥ ቁልፍ የውጊያ መሣሪያ ሆኖ ተከስቷል።

በኢትዮጵያም በተደረጉና በቀጠሉ ውጊያዎች ድሮን ወሳኝ የውጊያ መሣሪያ ከሆነ ሰነባብቷል። በሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት የትግራይ ኃይሎችን ወደኋላ የመለሰውና የጦርነቱ የኃይል ሚዛን ወደ ፌዴራል መንግሥት እንዲያጋድል ያደረገው አንዱ ምክንያት የድሮን ጥቅም ላይ መዋል እንደሆነ በሰፊው ሲነገር ነበር።

እ.ኤ.አ. ከ2020 ወዲህ ባሉት ዓመታት በሰፊው በመላው ዓለም በሚካሄዱ ውጊያዎችና የጦር ዘመቻዎች ላይ ጥቅም ላይ እየዋለ የሚገኘው ድሮን፣ አሁን ደግሞ ከመንግሥታት እጅ ወጥቶ በታጠቁ ኢመደበኛ ኃይሎች ወይም በአሸባሪዎች እጅ እየገባ

ረው ኅዋዊ (Policy Center for the New South) የተባለው ... አንድ የቅርብ ጊዜ ጥናት፣ በአፍሪካ ቢያንስ ከስድስት ያላነሱ የሽብር ቡድኖች የድሮን መሣሪያ መታጠቃቸውን ገልጿል።

ጃማ አትሙስራት አል ኢስላም ዋል ሙስሊም (JNIM) የተባለው በማሊ፣ በቶጎና በቡርኪና ፋሶ ተደጋጋሚ የድሮን ጥቃት የሚያደርሰው የሽብር ቡድን በቀዳሚነት ተጠቅሷል።

ኢስላሚክ ስቴት ኢን ዌስት አፍሪካ ፕሮቪንስ (ISWAP) ሌላው ድሮን የታጠቀ ኃይል መሆኑ ተነግሯል። ኢስላሚክ ስቴት ሳህል (Is Sahel) እንዲሁ ድሮን ይጠቀማል።

በናይጀሪያ የሚታወቀው ቦኮ ሀራም የሽብር ቡድንም ቢሆን በድሮን ዘመቻ በማካሄድ ስሙ ይነሳል። ኢስላሚክ ስቴት ኢን ሴንትራል አፍሪካ ፕሮቪንስ (ISCAP) የተባለውም ኃይል ድሮን የታጠቀ መሆኑ ይነገራል።

ከእነዚህ በተጨማሪ ደግሞ ኢትዮጵያን ጨምሮ ለመሳው የምሥራቅ አፍሪካ አገሮች የሥጋት ምንጭ የሆነው የሶማሊያ የሽብር ቡድን አልሸባብም ቢሆን፣ ድሮን በእጁ ያስገባ አደገኛ የሽብር ኃይል መሆኑ ይስማል።

የፖሊሲ ሴንተር ፎር ዘ ኒው ሳውዝ ተቋም ሰነድ እንዳመለከተው እነዚህ ሁሉ የአፍሪካ አኅጉርን እያመሱ ያሉ ኃይሎች ድሮንን ለስለላ፣ ለፕሮፓጋንዳም ሆነ ለግድያና ለማሸበር እየተጠቀሙት ይገኛሉ። በጦር ካምፖችና ማሠልጠኛዎች፣ በመንግሥት ተቋማት፣ በሲቪል መሰብሰቢያ



የአፍሪካ የድሮን አምራቾችና ተጠቃሚዎችን በአጋዝ የሚያሳይ ሰንጠረዥ (ምንጭ አፍሪካ ሴንተር ፎር ኒው አሜሪካን ሴኪዩሪቲ)

ቦታዎችና በሌሎችም አካባቢዎች ቡድኖቹ በድሮን ጥቃት ይከፍታሉ። እ.ኤ.አ. ከ2023 ጀምሮ በአፍሪካ አሸባሪዎች በድሮን ጥቃት መፈጸማቸው መመዝገቡንና ከ2024 አጋማሽ ወዲህ ደግሞ ይህን መሰሉ ጥቃት ቁጥሩ ማየሱን ይጠቅሳል። በተለይ እንደ ጄኒም (JNIM) ያሉ ቡድኖች ይህን ቴክኖሎጂ በሰፊው በማዋል ምዕራብ አፍሪካን ማመሳቸው ተመላክቷል።

ከቡርኪናፋሶ እስከ ኢትዮጵያ በርካታ የአፍሪካ መንግሥታት ከቱርክ፣ ከኢራን፣ ከቻይናና ከሌሎች አገሮች የድሮን ቴክኖሎጂን በሰፊው በመሸመት የጦር ኃይላቸውን አጠናክረዋል። ይሁን እንጂ በተቃራኒው

መንግሥታቱን የሚወጉ ታጣቂ ቡድኖችም ድሮንን በሌላ መንገድ በእጃቸው እያስገቡ መሆናቸው ይነገራል። አሁን ድሮን በአፍሪካ አሸባሪዎች ጭምር የታጠቁት አደገኛ መሣሪያ ሆኗል የሚለው ሪፖርቱ፣ ይህ ደግሞ መላው አኅጉሩ አዲስ ዓይነት የደኅንነት አደጋ መጋፈጥ መጀመሩን ያረጋገጠ ነው ይላል።

‹‹United Nations Institute for Disarmament Research›› (UNIDIR) የተባለው የተመድ ተቋም የቅርብ ጊዜ ሪፖርት ደግሞ፣ የድሮን ቴክኖሎጂን የሚጠቀሙ የታጠቁ ኃይሎችን ቁጥር በዛ አድርጎ ይጠቅሳል።

የሞዛምቢክ አህሉ ሙስሊም ... (ASWJ)፣ ያሉ ታጣቂ ቡድኖች ድሮን መታጠቃቸውን ይገልጻል።

በተለይ የሶማሊያዎቹ አልሸባብና አይኤስ ሽማቂዎች ይህንኑ መሣሪያ መገልገል መጀመራቸውን በሰፊው ያወሳል። እ.ኤ.አ. ከ2020 ጀምሮ አልሸባብ ድሮን በሰፊው ሲጠቀም ቆይቷል። ከሶማሊያ አልፎ ወደ ኬንያ ድንበር ዘልቆ ገብቶ ጭምር ድሮን ተጠቅሟል። ድሮኑን የታጠቀው ደግሞ በድብቅ አስገብቶና ለሲቪል አገልግሎት የሚውሉ ድሮኖችን ከገበያ ገዝቶ ጭምር ነው ይላል። እ.ኤ.አ. በ2025 የካቲት በጋልሙዱግ የሶማሊያ ሠራዊት ላይ ሁለት የአልሸባብ ድሮኖች ጥቃት ከማድረሳቸው በፊት ማክሸፉን ያጣቀሰው ሪፖርቱ፣ አሸባሪው ቡድን በድሮን ራሱን አዲሱ ከባድ የደኅንነት ሥጋት የሚለው ሪፖርቱ፣ በርካሽ ቴክኖሎጂው መገኘቱ ተመራጭ አድርጎታል ሲልም ያብራራል።

በድሮን ቴክኖሎጂ መጠቀም የአፍሪካ አሸባሪዎች ከውጭ ወይም ከመካከለኛው ምሥራቅ ሽማቂዎች ጋር ጥብቅ አጋርነትና ትብብር የፈጠሩበት ዘርፍ መሆኑ ይነገራል። በመካከለኛው ምሥራቅ ያሉ አሸባሪዎች ብቻ ሳይሆኑ የተለያዩ የጂኦ ፖለቲካ ፍላጎት ...

የኢትዮጵያ ወታደሮች የድሮን ማብረሪያ ሥልጠና በቻይና ቤጂንግ ሕዚዩሽን ትምህርት ቤት ሲከታተሉ (ምንጭ ዚ ኑዋ)

ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ አህመድ (ዶ/ር)፣ ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ እያደረገች ያለውን ዝግጅት ጠቁመዋል። ‹‹አንድን አገር በጠንካራ መሠረት ላይ ከሚያቆሙ ምሰሶዎች መካከል አንዱ የኢኮኖሚ ሰውጥ ነው። የጀመርነው የኢኮኖሚ ሪፎርም ለአጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገቱ መስመር መያዝ ወሳኝ ነው። ቀጥሎ ሊታሰብበት የሚገባው የአገር መሠረት የሆነ ጉዳይ ደግሞ የወታደራዊ አቅም ግንባታ ነው። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮች በቅደም ተከተል ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ወታደራዊ አቅም መገንባትን ማሳካት ካልቻሉ አደጋ ይገጥማቸዋል፤›› የሚል ይዘት ያለው ንግግር አስምተው ነበር።

ነው። እነዚህ የኢትዮጵያን ህልውናና ሉዓላዊነት የሚገዳደር አደጋ ሲገጥሙን አውጥተን በመጠቀም፣ ህልውናችንና የጀመርነውን ብልፅግና ለማስጠበቅ የምናውላቸው ይሆናል። በእርሻና በማዕድን ያመጣነው ስኬት በእንዲህ ዓይነት አቅም ካልተደገፈ ብዙ ባንዳና ባዳ ባለበት አካባቢ የአገር ጥቅምን ማስጠበቅ ከባድ ይሆናል፤›› በማለት ነበር ያብራሩት።

ድሮንን ጨምሮ በቴክኖሎጂ ዘርፍ የተጀመረው ለውጥና ዕድገት በአጭር ጊዜ አስደማሚ ውጤት የመጣበት መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠቁመዋል። በየጊዜው እየተቀየረና በፍጥነት እየተሰወጠ ካለው የዓለም የጦርነት ሥልትና የጦር ቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር አብሮ የሚሄድ የመከላከያ አቅም የመገንባት ጉዳይ፣ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮች በወቅቱ የተጋፈጡት ከባድ ኃላፊነት ሆኖ ነው የሚገኘው ብለዋል።

በቅርቡ የወጡ ሪፖርቶች በሦስት ዓመታት ብቻ በአፍሪካ በታጠቁ ኃይሎች በተፈጸሙ 50 የድሮን ጥቃቶች 1,000 ሰዎች ሲገደሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ደግሞ ቆስለዋል ተብሏል። ከቱርክ፣ ከቻይናና ከኢራን የሚገቡ ድሮኖች በአኅጉሩ መበራከታቸውንና የታጠቁ ቡድኖች በርካሽ እየዝቡ ለጥቃት እንደሚገለገሉባቸው ሲዘገብ ቆይቷል። በሱዳን፣ በኢትዮጵያ፣ በቡርኪና ፋሶ፣ በማሊ ግጭቶት ውስጥም ድሮኖች ጥቅም ላይ መዋላቸው ተነግሯል።

የስቲፍትንግ ጥናት ተቋም

ኃይገፐ ኃይሎተም ልክ እንደ አልሸባብ፣ አይኤስና ቦኮ ሀራም ሁሉ ድሮን እንደሚጠቁሙ ሪፖርቱ ያረጋግጣል።

በአፍሪካ አኅጉር በሊቢያ ጦርነት፣ በኢትዮጵያና በሱዳን እየተካሄዱ ባሉ የእርስ በእርስ ጦርነቶች ድሮን በሰፊው ለውጊያ አገልግሎት መዋሉ ይታወቃል። ይሁን እንጂ ዋና ግባቸው ማሸበር ወይም በሕዝብና በመንግሥት ላይ አደጋ መጣል የሆነ ኃይሎች ድሮን መጠቀም መጀመራቸው፣ አዲስና ያልተለመደ ክስተት መሆኑን ነው ሪፖርቱ ያተተው።

አ.ኤ.አ. ከ2018 ጀምሮ የሶማሊያው አልሸባብ ቡድን ትንንሽ ድሮኖችን በመጠቀም የፕሮፓጋንዳ መልዕክቶችን መበተን ጀመረ። በሒደት ደግሞ የመንግሥትና በሶማሊያ የተሰማሩ የውጭ ሰላም አስከባሪ ኃይሎችን እንቅስቃሴ መከታተል ሥራው ሆነ። ቡድኑ ከ2021 ጀምሮ እጅግ አነስተኛ በራሪ አካላትን በወታደራዊ ካምፖችና ተቋማት አካባቢ በመልቀቅ የስለላ ሥራ በሰፊው መሥራቱን ሪፖርቱ ቢጠቅስም፣ ነገር ግን እንደ ሌሎች ሽብር ቡድኖች እስከ ቅርብ ጊዜ ድርጊን ሰጥቃት ሲያውል አለመታየቱን ነው የሚገልጸው። አልሸባብ በየመን ከሚንቀሳቀሰው የአልቃይዳ ክንፍ ጋር ጥብቅ አጋርነት ያለው መሆኑ ቴክኖሎጂውን በቀላሉ ለማግኘት አማዞታል ተብሏል።

ግሎባል ኔትወርክ ኦን ኤክስትሪሚዝም ኤንድ ቴክኖሎጂ (GNET) ተቋም ያወጣው ሪፖርት በቡርኪናፋሶ፣ በዴሞክራቲክ ኮንጎ፣ በኬንያ፣ በሊቢያ፣ በማሊ፣ በሞዛምቢክ፣ በናይጄሪያ፣ በሶማሊያና በሱዳን በአጠቃላይ በዘጠኝ የአፍሪካ አገሮች ከመንግሥት ውጪ ቴጣው ዘፑንተሣንድ ዘፊል ራስ ገዝ አስተዳደር በክሊ ሚስካት ተራሮችና ዋሻዎች የመ ውን የአይኤስ ቡድንን የሚበተሰው ሪፖርቱ፣ ይህ ኃይል ከኢራቅና ከሶሪያ አይኤስ ሽማቂዎች ዕገዛ የሚያገኝና በድሮን ጥቃትም ራሱን ያጠናከረ መሆኑን ይጠቁማል። አሜሪካ ጭምር የዚህ ቡድን የድሮን ጥቃት በቀጣናው የፈጠረው አደጋ ሥጋት ውስጥ ከቷት፣ በፑንትላንድ ግዛት የተለያዩ የኃይል ተልዕኮዎችን ማካሄድ መጀመሯንም ሪፖርቱ ይጠቁማል።

የእነዚህንና ሌሎች በአፍሪካ ያሉ የሽብር ቡድኖችን በድሮን መሣሪያ የመደራጀት አቅም የመዘነው ግሎባል ኔትወርክ ኦን ኤክስትሪሚዝም ኤንድ ቴክኖሎጂ፣ ጉዳዩ ለአፍሪካ መንግሥታት ጠንካራ የደኅንነት ሥጋት ነው ይለዋል። የሽብር ቡድኖቹ በድሮን ጥቃት ለመፈጸም የሳተላይት ኢንተርኔትና የማይጠለፍ የመገናኛ ዘዴ ይጠቀማሉ። ድሮኖቹ ከራዳር ዕይታ ወይም ከመጥለፊያ ሞገድ ውጪ ሆነው ውጤታማ ጥቃት እንዲያደርሱ የሚያስችል ቴክኖሎጂም ታጥቀዋል ይላል። በዚህና በሌሎችም ምክንያቶች የተነሳ ለወትሮውም በቂ የፀረ ሽብር መከላከል አቅም ያነገቡ የአፍሪካ መንግሥታት ላይ ከባድ የደኅንነት ሥጋት ቡድኖቹ እንደፈጠሩ ነው ሪፖርቱ ያተተው።

አፍሪካ ዲፌንስ ፎረም በቅርብ ሰሞን ሀተታው በፑንትላንድ ግዛት የፀጥታ ኃይሎች ባካሄዱት ፍተሻ ፈንጂና ቦምብ ከሰማይ ማዝነብ የሚችሉ ድሮኖች በጭነት መኪና ከጋሮዌ ተጭነው ሲጓዙ ተይዘዋል ይላል። እነዚህ ድሮኖች የየመን የሁቲ አማፂያን ከታጠቋቸው ድሮኖች ጋር ተመሳሳይ መሆናቸውን የጠቀሰው ሥርዓሞተ ዘአገንሩ አንዲጨምር ማድረጋቸው ይጠቀሳል።

የአፍሪካ አገሮች ድሮን የታጠቁ ሽማቂ ቡድኖች በመጨመራቸው አዲስ ሥጋት መጋፈጣቸው በአሳሳቢነት እየተወሳ ነው። ይህ ቴክኖሎጂ እየዘመነና በሰው ሠራሽ ማገናዘቢያ (AI) ወደ የሚታዘገዘበት ምዕራፍ እየተሸጋገረ መሆኑ ደግሞ ተጨማሪ አሳሳቢ አደጋ እየተባለ ነው። በዩክሬንና በሩሲያ ጦርነት ራሳቸው ዒላማ መርጠው፣ መረጃ ተንትነውና ጠላትን ለይተው የሚተኩሱና አደጋ የሚያደርሱ ትንንሽ ድሮኖች ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው። የጊዜ ጉዳይ እንጂ እነዚህ ቴክኖሎጂዎች ወደ አፍሪካ መግባታቸው የማይቀር መሆኑን አንዳንድ ሪፖርቶች ይተነብያሉ። የአሸባሪ ቡድኖቹን የገንዘብና የቴክኖሎጂ ምንጭ ከወዲሁ ማድረቅ ካልተቻለ፣ የአፍሪካ አገሮች በቴክኖሎጂ ውጊያና የሽብር ጥቃት ወደለየለት ቀውስ እንደሚገቡ ነው እየተሠጋ ያለው።

ድሮን በመታጠቅና በሰፊው ለውጊያ በማዋል በአፍሪካ ስሟ ከቀዳሚዎቹ ተርታ የሚጠቀሰው ኢትዮጵያ፣ ለዚህ መሰሉ አዲስ ዓይነት የደኅንነት ሥጋት ምን ያህል ተዘጋጅታለች የሚለው ጉዳይ በሰፊው ይነሳል። ኢትዮጵያ በድሮን መታጠቅና መጠቀም ብቻ ሳይሆን ድሮን ወደ ውጭ ይልካሉ ከሚባሉ አገሮች ተርታም ትጠቀሳለች። ይሁን እንጂ አፍንጫዋ ሥር እንደ አይኤስና አልሸባብ ያሉ ቡድኖች ድሮን ታጥቀው እየተጠቀሙ መሆናቸው ለኢትዮጵያ ከባድ የፀጥታ ሥጋት መሆኑ እንደማይቀር በሰፊው ይነገራል።

በቅርቡ የድሮን ማምረቻ ፋብሪካ ሲጎበኙ ይህንኑ ሥጋት ጉዳዮች ቀጥሎ የሚመጡ ብለው የባህል፣ የቋንቋ፣ የሙዚቃና የመሳሰሉ ዕ ትችን የማሳካት አስፈላጊነትን ዓብይ (ዶ/ር) ጠቅሰው ነበር። በግብርና በኢንዱስትሪ፣ በቴክኖሎጂ፣ በቱሪዝም፣ በማዕድንና በሌሎችም መስኮች ኢትዮጵያ ከፍተኛ ለውጥ እያመጣች መሆኑንና የአገሪቱ የመበልፀግ አቅም ትልቅ መሆን አውስተዋል። ይህ ሁሉ ደግሞ በወታደራዊ አቅም ግንባታ ማጠናከር መታገዝ እንዳለበት አመላክተዋል።

‹‹አጥፍተው የሚጠፉ ድሮኖች በከፍተኛ ቁጥር እያመረትን ነው። በጅምላ (Swarm) መልክ ዘምተው ባደጉት አገሮች እንደምንሰማው የጠላትን ስብስብ ማጥፋት ይችላሉ። ሁሉተኞቹ ለስለላ የሚሆኑ ሲሆን በኪስና በቦርሳ ጭምር እካባቢያቸውን በሚገባ የሚቃኙ ናቸው። በቅርቡ የታየው የድሮን ትርዒት የሚካሄደው በእነዚህኞቹ ድሮኖች ነው። ለገበያ ጭምር በሰፊው ሊውሉ የሚችሉ ናቸው። ድሮን እዚህ በኢንሳ ይመረታል፣ በአየር ኃይል ይመረታል፣ በብሔራዊ መረጃና ደኅንነት ይመረታል። አቅማቸው የተለያዩ ድሮኖችን በተለያዩ ቦታዎች እናመርታለን፣›› በማለት አገሪቱ በሰፊው ወደ ድሮን ማምረት ዘርፍ መግባቷን ይፋ አድርገው ነበር።

ዓብይ (ዶ/ር) ለዚህ ዘርፍ አገሪቱ ትኩረት የሰጠችበትን መነሻም አብራርተው ነበር። ‹‹ከጥቂት ዓመታት በፊት ድሮን መታጠቅ ቀርቶ መግዛትም ፈተና ነበር። ገዝተን መጠቀም ከጀመርን በኋላ በተለያዩ ደረጃዎች ማምረት ጀምረናል። ለንግድ፣ ለስለላና፣ ለወታደራዊ የሚሆኑ በርካታ ድሮኖች እያመረትን በድሮን ለሚካሄዱ ውጊያዎችና ግጭቶች ዋና የቴክኖሎጂ ምንጭ መሆናቸውን ይገልጻል። ሞደርን ዋር ኢንስቲትዩት አት ዌስት ተቋም እንደከተበው ከሆነ፣ በቀደመው ጊዜ እንደ አሜሪካ ያሉ አገሮች ነበሩ በአፍሪካ በሚያካሂዷቸው የፀረ ሽብር ዘመቻዎች ድሮን የሚጠቀሙት። አሁን ይህ ተሰውጦ ራሳቸው የአፍሪካ መንግሥታት ዋና የድሮን ገዥ፣ አምራችና ተጠቃሚ ሆነዋል ይላል።

ድሮን ከውጭ በመግዛት ረገድ ናይጄሪያ ከዓለም 14ኛ፣ አልጀሪያ 15ኛ፣ እንዲሁም ኢትዮጵያ 12ኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ሪፖርቱ ይጠቅሳል። ከአፍሪካ አገሮች ድሮን ወደ ውጭ የሚልኩትን ማንነት ሲዘረዝር ደግሞ ግብፅ፣ ሱዳን፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ናይጄሪያ፣ ኬንያና ኢትዮጵያ እንደሚገኙበት ገልጿል። እነዚህ አገሮች የአፍሪካን 12 በመቶ የድሮን አቅርቦት እንደሚሸፍኑ ነው ያመለከተው። ጥናቱ አክሎም አ.ኤ.አ. በ2020 ብቻ 31 የድሮን ጥቃቶች በአፍሪካ የተፈጸሙ መሆናቸውንና 69 ሰዎች መገደላቸውን ያስረዳል። በ2024 ግን ይህ በእጅጉ አድጎ በአጠቃላይ ሰ484 ጊዜያት የድሮን ጥቃት መፈጸሩን፣ የሞቱ ሰዎች ቁጥርም ወደ 1,176 አድጓል ይላል። በአፍሪካ የድሮን ውጊያና ዕልቂት እየተበራከተ ነው በሚባልበት በዚህ ወቅት ደግሞ የጦርነት ሕግ የማይገዛቸው፣ ተጠያቂነትም ሆነ ኃላፊነት የሌለባቸው አሸባሪና የታጠቁ ኢመደበኛ ቡድኖች ይህን መሣሪያ መታጠቅ መጀመራቸው አገሮቹ የተጋፈጡትን አደጋ ጨምሮታል ተብሏል።

አዲስ ዘመን

ኦፕ

ማክሰኞ 84ኛ ዓመት ቁጥር 294 ሰኔ 24 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 34.50 ብዕረ ፣ ነ ለስ ንሃ ጽ ያ ህዳሴ ይ ተ ጋ!

የኅብረተሰቡን የኤሌክትሪክ ተጠቃሚነት 65 በመቶ ለማድረስ እየተሠራ ነው

- ሀገሪቱ ያልተጠቀመችው ከ150 ገጋ ዋት በላይ የታዳሽ ኃይል አቅም አላት

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፦ በ2030 በብሔራዊ ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራም ምክት 65 በመቶ የሚሆነውን የኅብረተሰብ ከፍል የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ። ኢትዮጵያ ከፀሐይ ኃይል፣ ከውሃ፣ ከንፋስ እና ከከርሰ ምድር ሙቀት ያልተጠቀመችው ከ150 ጊጋ ዋት በላይ የታዳሽ ኃይል አቅም አላት ተብሏ።

በሚኒስቴሩ የኢነርጂ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ኢንጅነር ስለሺ ግዛ (ዶ/ር) ለአዲስ ዘመን እንደገለፁት፣ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ተደርጎበትን ኃብት ለመጠቀም

ኃይል ሌጂ...

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከዓለም አቀፍ የአቶሚክ ኃይል ኤጀንሲ (IAEA) ዋና ዳይሬክተር ማሪያኖ ግሮሲ ጋር መወያየታቸውን አረታወቁ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ትናንት በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት ጽሑፍ እንዳስታወቁት፣ በሬይስ ኦፍ ሆፕ ገብዔ ለመሳተፍ አዲስ አቡ፣ ከጠቡት የዓለም አቀፍ የአቶሚክ ኃይል ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ማሪያኖ ግሮሲ ጋር ተወያይተዋል።

ውይይታቸው የዓለም አቀፉ አቶሚክ ኃይል በኢትዮጵያ የሚያደርገው ድጋፍ፣ በካንሰር ሕክምና ከብካቤ፣ የአንስሳት ጤና፣ የዜጌ ፍላይ ማጥፊያ፣ በኒውክሌር ኢንጂነሪንግ እና የቁጥጥር ማሕቀፎችን ጨምሮ ወደፊት በሚኖሩ የትብብር አድሎች ላይ ያተኮረ እንደነበር አመልክተዋል፡፡

ኢትዮጵያ የዜጎቿን የኃይል ፍላጎት ሰማኃላት ንጹሀና ታዳሽ ኃይል በማልማት ላይ እንደሆች ያመለከቱት ኃላፊው፣ የኃይል አቅርቦቱን በሚፈለገው ልክ ተደራሽ ለማድረግ የፖሊሲ ማሻሻያዎች መደረጋቸውን ጠቁመዋል ።

የኃብረተሰቡን የልልክትሪክ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ኢራን የኒውክሌር ጦር መሳሪያ ባለቤት እንድትሆን እንደማይፈቅዱ ትራምፕ ዳግም አስታወቁ

ገጽ 4

"ሕይወት አድን የሕክምና ቴክኖሎጂዎችን ተደራሽ ለማድረግ እየተሠራ ነው"

- ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ሕይወት አድን የሕክምና ቴክኖሎጂዎች ተደራሽ የማድረግ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ ገለጹ። ከ70 በመቶ በላይ የሚሆነው የካንሰር ሞት ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት እንደሚከሰት ተጠቆመ።

"ሬይስ ኦፍ ሆፕ 2025" ጉባኤ ትናንት በአዲስ አበባ ሲጀመር፤ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር፤ ኢትዮጵያ የኒውክሌር ሳይንስ ላይ ኢንቨስት እያደረች ነው። የጨረር ሕክምና አገልግሎቶችን በብዙ የሀገራችን ክልሎች እያስፋፋ ነው፡፡

የኒውክሌር ሳይንስ ላይ እየሠራን ያለነው ለሕክምና እንክብካቤ ብቻ ሳይሆን አስቀድሞ ለመቆጣጠር እና ለመከላከልም ጭምር ነው ያሉት አቶ ተመስገን፤ በኢትዮጵያ ታክሞ በሚድን የካንሰር በሽታ አንድም ሰው እንዳይሞት ሕይወት አድን የሕክምና ቴክኖሎጂዎች ተደራሽ የማድረግ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

"ሕይወት አደን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል